የክብሩ ወራሾች

አምላከ አማልክት የሰማዩ ንጉስ

ፍጥረቱን ሊመግብ ካዘጋጀው ድግስ

መጠተው ሊሳተፉ መአዱን ሊቆርሱ

ብርሃን ተጎናጽፈው ብርሀንን ለብሰው

ዳግመኛ በደስታ በክብር ሲነሱ

የእሳቱን ጽና በላይ በሰማያት በብርሃን ደምቀው

የእሳቱን ጽና ነበልባሉን ይዘው

በቅዱስ መንፈሱ ዝማሬ ተሞልተው

ሀሌሉያ እያሉ በአንድ ሊዘምሩ ክብሩን ሊያስተምሩ

በአዋጅ የጠራቸው ብዙዎች ነበሩ

ግና..... ጥሪውን አክብረው ከቤቱ የተገኙ ምርጦች ብቻ ቀሩ

ጥቂቶች እናንተ ቤቱ የመጣችሁ

ለጸጋ ለድህነት ለክብር የጠራችሁ

ወዲያ በስጋችሁ ወዲህ በነፍሳችሁ

ከብዙዎች መርጦ ለዚህ ያደላችሁ

እንኳንስ በሰላም በደህና መጣችሁ

ጥሪውን ሰምታችሁ ከርሱ ጋር ልትኖሩ

ነገረ ወንጌሉን ቃሉን ልትማሩ

የህይወትን ምግብ ከርሱ ልትሸምቱ

የመጣችሁ ሁሉ.....

እዚህ ከኛ ጋራ በመልካሙ ቦታ በመልካሙ ስፍራ

ተቀምጠን በህብረት በአንድነት በጋራ

ስሙን ስንቀድስ ክብሩን ስናወራ

በደስታ በእልልታ ከልብ ስንዘምር

ቅኔ ውዳሴውን ወንጌሉን ስንማር

ገድለ ቅዱሳንን አስበን ስንዘክር

በዘውትር ጸሎት በጠዋት ቅዳሴ ቆመን ስናስቀድስ

ጸሎት ሰአታቱን ኪዳኑን ስናደርስ

ተግታችሁ መታችሁ ቃሉን ገብይታችሁ

ዝናብና ብርዱን ቁሩን ታግሳችሁ

ከመምህሮቻችሁ እግር ስር ቁጭ ብላችሁ ተምራችሁ

ለዛሬይቱ ቀን የበቃችሁ

ይገባቹሀልና አንኳን ደረሳችሁ

ግና..... ያልታደሉት ወድያ በጨለማ ተሰውረው ያሉት

ለዚህኛው ጥሪ ትኩረትን ያልሰጡት

የዚያን ወዲ ጥሪ ጩኸትን አድምጠው

አሳሳች ትምህርቱን ከልባቸው ሰምተው

ተነስተው የሄዱት ሞት የሞት ሞትን ጉዞ "ሀ" ብለው ጀመሩት

ጥቂቶች እናንተ ቤቱ የመጣችሁ

በአንድነት በፍቅር በእምነት ጸንታችሁ

ከምርጦቹ መሃል ከዚያ ተገኝታችሁ

የክብሩ ወራሾች ለመሆን ያብቃችሁ

.....*ተፃፈ- በ ወልደሰማእት* .....